# በቀልድ ምርጫ  መሳተፍ ትርጉሙ  ምንድ ነው?

ይልማ በቀለ

ውድ ወንድሜ አቶ ግርማ ካሳ ያቀረቡትን ጽሁፍ በአዲስ ቮይስ ድረ ገጽ ላይ አንብቤዋለሁ፡[i] አቶ ግርማ  ካሳ በየጊዜው  በዳያስፖራ ድረ ገፆች ላይ በአለው የአገራችን ሁኔታ የሚጽፉትን ተከታትዬ አነበዋለሁ። ጊዜአቸውን ውስደው ፤በጥሞና አስበው  የሚአወጡት ጽሁፍ አንባቢዎቻቸውን ስለ ውድ አገራችን እንድናስብ ያበረታታናል ብየአምናለሁ።

ዛሬ ግን እኔ ማተኮር የፈለጉት ሰሞኑን በጻፉት “**የፊታችን ምርጫ  ቀልድ ነው - መድረኩ ግን መሳተፍ ይበጀዋል**”  በተባለው  ላይ ነው ። (ከዚህ ጽሁፍ መጨረሻ ላይ ያለውን ሊንክ ቢጫኑ የአቶ ግርማን ጽሁፍ ለማንበብ ይችላሉ)

ጽሁፉን የሚጀምሩት ‘ሕወሃት ነፃና ፍትሃዊ ምርጫ ለማድረግይዘጋጃል ታዛቢዎች አዲስ አበባ ገብተዋል፣ መድርክ፣መኢአድ፣ ኢዳፓ፣ የምርጫ ዘመቻው አጧጥፈውታል ብለው ነው። አስደሳች ጉዳይ ነው።

ስለ ዳያስፖራው ደግሞ ሲናገሩ ግንቦት ሰባትና አንዳንድ ተቋዋሚዎች ‘ምርጫውን ሕወሃት ስላሸነፈው ያለመሳተፍና እራስን ማግለል‘ የሚል የፕሮፓጋንዳ ዘመቻ ከፍተዋል’ ይላሉ።እነፕሮፌሰር መስፍንና ደጋፊዎቻችው  ደግሞ እንዴት ወ/ሮ (ሊቀመንበር) ብርቱካን ታስራ ምርጫ ይገባል የማለት ጥያቄ እያነሱ መሆናችቸውን ይገለፃሉ።

የፅሁፋቸውም አላማ  ውይይት ለማምጣት መሆኑን ይገልጹና መደምደሚያው ላይ ‘በምርጫው መሳተፍ አይገባም  የሚል አቋም የሚይዙ ወገኖች ካሉ ደግሞ የመከራከሪያ ነጥባቸውን ለመስማት ዝግጁዎች ነን። አንድ ሁለት ብለው የምርጫውን ቦይኮት ጥቅም  ያስርዱን። ያላቸውን አማራጮች ያቅርቡልን። መክሰስ፣ መተቸት፣ መሳደብ በጣም ቀላል ነው። መፍትሂ ማምጣት ግን ፍፁም የተለየ ነገር ነው። ሌሎች ድርጅቶች የሚሰሩትን ማጣጣል አንድ ነገር ነው። ሰርቶ ማሳየት ግን ሌላ ነገር ነው’ ብለው  ሃይል በተሞላው  ግሳፄ ይዘጋሉ።

በጣም ጥሩ አቶ ግርማ እኔም በበኩሌ በጣም እስማማለሁ። በኔ አስተሳሰብ ይሄ ጽሁፍ ለመጀመሪያ ጌዜ የመድረኩን አላማ  ከማድበስበስ አልፍ በግልጽ ያወጣ  ነው  ብዬ አምናለሁ።መድረኩ  ምን ይፈልጋል ይሚለውን ጥያቄ ለመጀመሪያ ጊዜ የሚመልስ ይመስላል።ባይመልስም ይሞክራል።

ወደ ዋናው ቁም ነገሩ እንሂድና ጽሁፉ የሕወሃትን መንግስት ተቋሚዎች በሙሉ የምንስማማባቸውን ነጥቦች ሲያቀርብ ዋና ብሎ የሚያስማማንም በቀይ ያስምርዋል ‘**የ2002 ምርጫን ከምንም መሳፍርት ሚዛን ፍትሓዊና ዲሞክራሲያዊ ሊባል አይችልም**’ ከዚህም አልፎ ያለውን ችግር ሲያብራሩ የወ/ት (ሊቀመንበር) ብርቱካን ያለ አግባብ መታስር፤ ብግልፅ የምናውቀው ሁለት እጩዎች መገደል፣ በምርጫው ምክንያት የብዙ ወገኖች መጎሳቆልና የመነግስት ሰርራተኞች በማስገደድ የመሃላ ፊርማ መደረጉን ገልፆ ‘**ይህ ሁሉ ምን ያህል ምርጫው ጫወታ መሆኑን በግልጽ የሚያሳይ ነው**’ ይላል።

ትንታነውን በመቀጠልም ሕውሃት እስከ አርባ ሺህ የምርጫ ጣቢያዎች በታዛቢነት የሚያገለግሉ አባሎቹን (ካድሬ) መለምኋል ማለትም ይላሉ አቶ ግርማ ‘**የምርጫውን ውጤት የሚወስነው ደግሞ ድምጽ ስጭው ሳይሆን ድምጽ ቆጣሪው ነው** ቢባል ሕወሃት የሚያደርገው ምርጫ በምንም ስፈርት ንጹህና ዲሞክራሲያዊ ሊሆን አይችልም ብሎ በሩን ይቀረቅራል።

ውድ አንባቢ ሆይ፣ ታድያስ ክርክሩ ምን ላይ ነው ብለው ትንሽ ቢቸገሩ አያስደንቅም። ምክንያቱም በፀሃፊው አነጋገር ሕውሃት ወይም የአቶ መለስ ድርጅት የዋናው ተቃራኒ ፓርቲ ሊቀመንበርን በግፍ አስሮ፤ የፓርላማ እጩዎችን ገድሎ፣ከሚኖሩበት አፈናቅሎ፤ ስልጣኑን በመጠቀም ሰራትኞችን የባርነት ቃል ኪዳን አስፈርሞና ካድሬዎቹን የምርጫ ታዛቢ ብሎ ሹሞ ለይስሙላና ፈረንጆችን ለመደለል በሚያደረገው  ምርጫ ላይ መሳተፍ ተገቢ ነው ብልው ክርክራቸውን ያቀርባሉ፣ ስምንት ነጥቦችም ያስቀምጣሉ።

‘ክርክሩና አለመስማማቱ የሚመጣው’ ይላሉ ፀሓፊው ‘ምርጫው …ኢፍትሃዊና ዴሞክራሲያ ሆኖም፣ ሕወሃት/ኢሕአዴግ በቀላሉ አጭበርብሮ ተመረጥኩኝ ብሎ የሚያውጅበት ሁኔታ ስፊ ቢሆንም፣ ከመርጫው እራሳችንን ማግለል ነው የሚበጀው ወይንስ በምርጫው ገፍቶ መሄድ? በሚለው ላይ ነው።

ፀሃፊው የሚሉን በምንም አይነት መንገድ የአቶ መለስ መንግስት የመሸነፍ ሃሳብ የለውም፤ መሬትና ሰማይ ቢገናኝ አይሸነፍም፣ ግን ቢሆንም ምን አለበት ገብተን ብንሸነፍ ነው። አቶ መለስ 'አይናችሁን ጨፍኑ ላታልላችሁ ፈልጋለሁ' ሲሉ ኩታ ማቀበል እንዴት መልካም ይሆናል ውድ ወዳጄ?

ግድ የለም እሺ ብለን እስቲ ፀሃፊው የዘረዘሩትን ስምንት ንጥቦች እንመልከታቸው።በመጀመሪያ የወያኔው መንግሥት በምርጫው ማግስት አሸነፍኩ ብሎ ሲያውጅ፣ ይላሉ ፀሃፊው ፣ የምእራብ መንግስታትና ሰብአዊ መብት ድርጅቶች ጥቂት ያወግዙና ይቀበሉታል፣ ስለዚህ 'መድረኩ ከምርጫው ቢወጣ የሚያገኘው አንዳች ፋይዳና ጥቅም አይኖርም'። ትንሽ ግራ የሚያጋባ አነጋገር ነው። ምርጫው የሚካሄደው በኢትዮጵያኖች ለኢትዮጵያውያን ከሆነ የፈረንጆች መቀበልና አለመቀበል በዚህ ውስጥ ምን አገባው። በሕወሃት መንግስት ሕገ ወጥ አገዛዝ እሳት የሚነደው ኢትዮጵያዊ ነው ወይስ ፈረንጅ? ታድያ መድረኩ መጨነቅ ያለበት ስለ ሕዝቡ ወይስ ስለራሱ? ትላንት ኬንያ ውስጥ የተጭበረበረ ምርጫ ሲካሄድ ፈረንጆቹኮ ተቀብለውት ሕዝቡ ነው እኮ አይሆንም ያለው።እስቲ በታሪክ ተበዳዩ ሳይጮህ ዳኝነት የተጠራበት ጊዜ ወይንም ቦታ ይነገረን?

በሁለተኛ ደረጃ ሕወሃት መኢአድንና፣ ኢዴፓን የመሳሰሉ ምርከኞች ስላሉት መድረኩ ብቻውን ይቀራል ስለዚህ መሳተፉ ይበጃል ነው።በጣም ደካማ ክርክር ይመስላል። ለመሆኑ ሕወሃት መቼ አጃቢ አጥትቶ ያውቃል? ጥያቄው አጃቢነት ለማን ጠቀመ ቢሆን ጥሩ ይመስላል።አልበቃ ተብሎ ደግሞ የደቡብ አፍሪካ ትግል ይጠቀሳል።ታድያ እኮ እነ ኔልሰን ማንዴላ፣ ስቲቭን ቢኮ ያስተማሩን ሌላ ነው። በሰላም ይመረጣል ካልሆነም በሰደፍ እንጅ ኩታ አቀብሉኝ አይኔን ልሸፍን አልወጣቸውም።

በአራተኛ ደረጃ መድረኩ እራሱን ቢያገል አገዛዙ ፀረ ሰላምና ሽብርተኛ በማለት ሕጋዊንቱን ይነጥቀዋል ስለዚህ በግልጽ መንቀሳቀስ፣ ስብሰባዎች ሰላማዊ ሠልፎች ማናቸውንም ዝግጅት ማድረግ አይችልም፣ ጽ/ቤቱም ይዘጋል ይላሉ። ችግሩ የህገወጥ መንግስትን ባሕሪን ካለመገንዘብ የመጣ ይመስላል። የፓርቲው ሕጋዊነት እኮ በህገ መንግስቱ ላይ የተመሰረተ ነው እንጅ በገዥው በጎ ፈቃድ የተሰጠ አይደለም፣ ስለዚህ የመድረኩ ስራ ገዥው የራሱን ህግ እንዲያከብር ማስገደድ ነው እንጂ እንደ ቄጠማ መሽመድመድ መሆን የለበትም።እውነቱ ግን መድረኩ ዛሬ ሕጋዊ ሆኖ ከላይ የተጠቀሱትን መች አደረገና? ለሊቀመንበርዋ አንድ አመት እስራት የሻማ ማብራት ዝግጅት ዝግ ቤት ውስጥ የተደረገው በሕገመንግስቱ የተፈቀደውን ለማስከበር ወደ ሁዋላ ስለተባለ አይደለም? በተራ ካድሬ ስብሰባ የሚከለከለው፣ ሽማግሌ አሮጊት የሚደበደበው ሃቅ ነው እኮ።

አምስተኛው ነጥብ ለቁጥር የገባ ይመስላል። መድረኩ አሁን 'የሚያደርጋቸው እንቅስቃሴዎች ምርጫውም ካለቀ ብኋላ እንዲቀጥሉ መደረግ አለበት' ይላል። ችግሩ ግን አሁን በምርጫ ሰበብ ፈረንጆቹ ባሉበት እንኳን ያለ ሕወሃት ፈቃድ መሰብሰብ ያልተቻለ ታድያስ ከምርጫው በኋላ የሚሆን ይመሰላል? ታዛቢ ይፍረድ። 'ኢሓአዴግ አሸነፈ ማለት ለሚቀጥሉት አምስት አመታት ይገዛል ማለት አይደለም' ሲሉ ምን ማለታቸው ይሆን?

ስድስተኛው ስለ ፈረንጆች መቀበል አለመቀበል ሰለሆን መጀመሪያው ላይ ያየነው መሰለኝ። ሰባተኛው ነጥብ በእውነት ላይ የተመረኮዘ አይመስልም። በመላው ፁሁፉ ሊቀመንበር ብርቱካን የምትጠራው ወ/ት ብርቱካን ተብላ መሆኑ ምክንያቱ አልገባኝም። ሆኖም መድረኩም ቢሆን አንድነት የሊቀመንበሯ አንደኛ ተሟጋች ናቸው ማለት እውነትን እንደማጣመም ይቆጠራል። በቅርብ ጊዜ እንኳ ሕመሟን ለአለም ያስታወቁት ወዳጆቿ ናችው እንጂ ጓዶችዋ ነን ባይዎች አይደሉም።በዳያስፖራውም የሊቀመንበሯን ጉዳይ በትጋትና ባለመሰልቸት የሚያካሂዱት በፈቃደኝነት የተቋቋሙት ድርጅቶች ናቸው እንጂ በሰሜን አሜሪካ ያለው የአንድነት ደጋፊ ቡድን አይደለም።

በስምንተኛ ቁጥር ላይ በተጠቀሰው አስተሳሰብ መስጠት ትንሽ ይቸግራል። እኔ እንደማውቀው ጌታ እግዚአብሄር ያለው እኔም እንድረዳችሁ መጀመሪያ እራሳችሁን እርዱ መሰለኝ። ታድያ እጅ አጣምሮ ቁጭ ብሎ 'ተአምር' መጠበቅ የት ያደርሳል? ማንም ኢትዮጵያዊ ይሄንን ምርጫ ፀሃፊው እንዳሉት 'እንደ ቀልድና ጫወታ' አይወስደውም። በሌላ በኩል አቶ ግርማ **"የፊታችን ምርጫ ቀልድ ነው"** ብለው ሲተቹ ብዙዎቻችን የምንስማማ ነን ብዬ አምናለሁ። በርግጥ ደግሞ የአቶ መለስ መንግስት ግን በሕዝቡ ብሶት ላይ እየቀለደ መሆኑን የአለም ህዝብ የሚያውቀው ይመስለኛል።

በኔ አስተሳሰብ 'መድረክ' በምርጫውን ለመሳተፍ ሙሉ መበት አለው ብየ አመናለሁ። የመድረክ መሳተፍ ግን የኢትዮጵያ ሕዝብ ካለበት መከራ የሚያወጣ መፍቻ ቁልፍ አለው ብየ አላምንም። የአገራችን ሰው ሲተረት 'የማያጠግብ እንጀራ ከምጣዱ ያሰታወቃል' ይላሉ። የመደረክም ጉዳይ እንደዛው ሁኖ አግኝቸዋለሁ። ባንድ በኩል 'የሰላማዊ ትግል' እያካሄድን ነው ይሉናል። ጠጋ ብሎ ሲታይ ግን ከመጽሃፉ አንድ ገጽ ብቻ ያነበቡ ይመስላሉ፣ ይኸውም ምርጫ ላይ ብቻ ያተኮረ ይመስላል። ታድያ እኮ 'የሰላማዊ ትግል' እነ ማሃተመ ጋንዲ፣

*ማርቲን ሉተር ኪንግ፣ ኔልሰን ማንዴላ ያስተማሩን ልዩ ነው። እነሱ የተጠቀሙት እኮ 'ካሮትና፣ ዱላ' የተባለውን መንገድ መሰለኝ። መድረኩ ብዙ ካሮት የጫነ ይመስላል ምናለ ዱላው ቢጠፋ አርጩሜ እንኳን ቢይዝ።*

*ሊቀ መንበሯ ወንጀለኛ ነች፣ እሺ ስብሰባ አየፈቀድም፣ እሺ ተወዳዳሪዎች ይገደላሉ፣ እሺ ወዘተ ወዘተ።*

*መቸስ አንድ ነገር ጥሩም ነው ወይም መጥፎ ለመባል መሞከር አለበት። እነ አቶ መለስ ስልጣን ከተፈናጠጡ ይኸው  ወደ አሥራ ስምንት አመት ሆኖታል። አሁን የሚደረገው  ምርጫ  አራተኛው ይመስለኛል። የኔ ጥያቄ የተቋዋሚው ጎራ ነን እያሉ የአቶ መለስ ፓርላማ ውስጥ የተሳተፉ አንዳንድ አሉ፣ እስቲ እንደው ለእነዚህ አዛውንቶች ስራ ከመስጠት በላይ የኢትዮጵያ ሕዝብ ምን ትርፍ አገኘ? እስቲ አሥራ ስምንት አመት አብሮ ከመስራት ያመጡትን ጥቅም ይንገሩን? እስቲ ያሳለፉት አንድ ሕግ ካለ ይጥቀሱልን? በማንም ያልተመርጠ ካድሬ መጫወቻ ከመሆንና ለሕወሃት ሌጅትማሲ ከመስጠት በስተቀር ሌላ ምን የሚያሳዩት አለ?*

*ከራሳችንና ከአለም ሕዝቦች ታሪክ ብንማር የሚከፋ አይመስለኝም። ለምሳሌ ፋሽሽት ጣልያን ውድ ሃገራችንን የደፍረ ጊዜ ቆይ እስቲ መጀመሪያ እንደራደርና ቀስ ብለን ሰጥ ብለን ተገዝተን እናስወጣዋለን አላልንም። አባቶታችን፣ እናቶታችን ጎበዝ ተነሳ አገርና ቤት ተደፍሮአል ነው ያሉት። አይ አሁን አቅም የለንም ቀስ ብለን እስክምንደራጅ መጠበቅ ይሻላል አልወጣችውም። ለነፃነት ቀጠሮ አይያዝም። ነውር ነው።*

*ታድያስ መድረኩ የሚለን ያለፈው አሥራ ስመንት አምት የተሞከረወንና ምንም ውጤት ያለመጣውን ለመስራት እድል ስጡን ነው? ዛሬ በምርጫው ያላሳዩትን ሀሞት ነገ ደሞዝተኛና ባለስልጣን ሲሆኑ ከየት ያመጡታል? የፈረንጆች አባባል 'ምራ፣ ተከተል ውይም ከመንገዱ ውጣ' የሚባለው እዚህ ቦታ ያለው አነጋገር መሰለኝ።*

*መደረኩን መለካም እድል እመኝለታለሁ። የመድረኩ መሪዎችን ቸሩ ፈጣሪአችን ይጠብቃቸው እላለሁ። ከሕወሃት ጋር መደራደር የነብር ጭራ እንደ መያዝ ነው፣ መጨረሻው  የሚያምር አይመስለም።*

---

i

([http://www.pdfdownload.org/pdf2html/view_online.php?url=http%3A%2F%2Faddisvoice.com%2Famh%2Felection_yes.pdf](http://www.pdfdownload.org/pdf2html/view_online.php?url=http%3A%2F%2Faddisvoice.com%2Famh%2Felection_yes.pdf))